# ወያኔዋ ትርፉ_ኪዳነማርያም በአውስትራሊያ የኢትዮጵያ_አምባሳደር_ጥገኝነት_ጠየቁ‼



ትርፉ_ኪዳነማርያም

በአውስተራሊያ የኢትዮጵያ አምባሳደር የሆኑት ወ/ሮ ትርፉ_ኪዳነማርያም በቅርቡ ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ ጥሪ ቀርቦላቸው ነበር። ይሁን እንጂ አምባሳደሯ ወደ አዲስ አበባ ከመምጣት ይልቅ እዛው አውስትራሊያ ውስጥ ጥገኝነት ጠይቀዋል። ከአውስትራሊያ በደረሰን መረጃ መሠረት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ ጥሪ ቢያቀርብላቸውም ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። አምባሳደሯ ጥገኝነት የጠየቁት የአምባሳዶር መኖርያ ቤት፣ የሚያሽከረክሩትን መኪና እና ሌሎች ንብረቶች በአግባቡ ሳያስረክቡ መሆኑን የመረጃ ምንጫችን ጠቁሟል።

አምባሳደር ትርፉ ኪዳነማርያም የቀድሞ የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ኣይተ አባይ_ወልዱ ባለቤት ሲሆኑ ከሁለት አመት በፊት ባለቤታቸው አቶ አባይ ወልዱ እና ወ/ሮ አዜብ መስፍንን ጨምሮ የመለስ ዜናዊ ቡድን የሆኑ የህወሓት ባለስልጣናት በአቦይ ስብሃት ቡድን ተገፍተው ከሥራ አስፈፃሚ አባልነት ሲባረሩ ተቃውመዋል። ይህን ተከትሎ መቀሌ ላይ የመሸገው የአቦይ ስብሃት ቡድን ፀረ_ለውጥ መሆኑን በመጥቀስ ማውገዛቸው ይታወሳል።

በመሆኑም ከአምባሳደርነት ከተነሱ ያላቸው አማራጭ ከብልፅግና_ፓርቲ ጋር በመተባበር መስራት አሊያም መቀሌ ገብቶ መመሸግ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። የመጀመሪያው አማራጭ ከአምባሳደሯ በተጨማሪ ባለቤታቸውን አቶ አባይ ወልዱን ጭምር ከብልፅግና ፓርቲ ጋር የሚያቀርብ ሲሆን መቀሌ በመሸጉት ህወሓቶች ቁስል ላይ ጨው የመነስነስ ያህል ነው። መቀሌ የመሸገው ቡድን በባለቤታቸውን ከስልጣን ያስወገደበት አግባብ፣ እንዲሁም ባለፈው አመት መቀሌ የመሸገውን ቡድን "ፀረ_ለውጥ፥ ፀረ-ህዝብ እና ዘራፊ" በማለት መወረፋቸው ሲታሰብ ህወሓት እስካለ ድረስ አምባሳደሯ መቀሌን እንደማረግጡ እርግጥ ነው። ከዚህ አጣብቂኝ ውስጥ የገቡት አምባሳደር ትርፉ ኪዳነማርያም በክብር የሹመት ደብዳቤያቸውን ባስገቡበት ሀገር ጥገኝነት ለመጠየቅ ተገድደዋል።

2020/06/11